# <u>አቤት ውሸት !!</u>

ጨቋኝ ስርዓቶች ከሀይልና አፈና ባልተናነሰ የሚተማመኑቡት ሕዝብን ማደናገሪያ መሳሪያቸው ውሸትና ቅጥፈት ነው። መገናኛ ብዙሃንን በቁጥጥራቸው ስር ያደርጉና ሀሰትን ያሰራጫሉ ። ወያኔ ደግም የዋሾዎች ዋሾና የቀጣፊ ቀጣፊ ነው ፡፡ ስለዚህም ወያኔ የሚያሰራጨው ውሸት ብዙና አንዳንዶንችም እያወናበደ ያለ ነው ። በቅርቡ ወያኔ ባስራጨው ሀሰት ለምሳሌ ማንንም በጋዜጠኝነቱ አላሰርንም ብሏል ። እነ እስክንድር ነጋና ርዕዮት ወደ እስር የተዳረጉት ዘፈን ሲዘፍኑ ነበር ማለት ነው። ውሸት! የዓለም ባንክም ኤኮኖሚዬ ማደጉን ምስክር ሆኗል ብሏልም ። ሌላ ምን ሊሉ ይጠበቅ ነበር ? ወያኔ የምዕራቦቹ ቡችላና ሎሌ ነውና ጌቶቹ አደገ ተመነደገ ብለው ቢዋሹሉት ማስገረም የለበትም ። ቡችላን ካላደነቁ ማንን ሊያመሰገኑ ?

ወያኔ በቅርቡ ባስደመጠን ልፈፋው ከደሙ ነጻ ነኝ ብሏል ። ይህን ሃቁ የሚቀበለው አይደለም ። ወያኔ በቀይ ሽብር ዋና ተሳታፊ ነበር ። ዛሬም ነጭ ሽብር እያለ የሚንጫጫው ፕሮፌሰር ለወታደራዊ ደርግ ስልጣን አትልቀቁ ብሎ የመከረውና ወያኔን በመሳሪያ ሊያወድቁ የሚታገሉትን የወነጀለው ነው። ሌላ የወያኔ መሳሪያ ነው ። ያሳዝናል። የሀገሪቷን ሀቅና ማንነት ወያኔ ደግም ደጋግሞ ክዶ ሌላ የሀሰት የብረዛ ታሪከን እያሰራጨ ነው ። ሀገርን ለማጥፋት በቅድሚያ ታሪኳን ማውደም የግድ ነው ። ለነጻነት የታገሉትን ሁሉ ማርከስ ግዳጃቸው ይሆናል ። በአሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያ የታገሉ ድርጅቶች ላይ የተከፈተውን ሰፊ ዘመቻ ያጤኗል! የውሸት ዘመቻው ለከት አልባ ነው። ወያኔ ጋዜጠኞችን አሰርክ ሲባል ፍጹም እያለ ነው። ማንም ጋዜጠኛ በስራውና ሙያው የተነሳ ከቶም አልታሰረም ይላል ወያኔ-- በሽብርተኛነት እንጂ! ወያኔ ለአፈናው አመቺ የሆነ ደምብና ህግ አውጥቷል። በዚህ ጸረ ሽብርተኛ ህጉ መሰረት ሰፈሯን የለቀቀች ድመትም መክሰስ ትችላለች ። ሀቁ ግን ብዙዎች መታሰራቸውና መጋዛቸው ነው ። የፖለቲካ እስረኖች ይፈቱ ለሚለው ጥያቄ ወያኔ ያለው መልስ አንድም ሰው ቢሆን በፖለቲካ ምክንያት አልታሰረም የሚል ነው ። በወያኔ ቋንቃ ፖለቲካ ወንጀል ነው ። ስለዚህም ወያኔን በፖለቲካ የተቃወመ ሁሉ ወንጀለኛ እንጂ ሌላ አይደለም ማለት ነው ። ወያኔ ክሶቹን በሀሰት ያጅባል--መሰረት የላቸውምና ። ባለፉት 22 ዓመታት ወያኔ ስንቴ ዋሽቷል፤ ስንቴስ ቀባርጧል? ከቁጥር በላይ ነው ። ውሎ አድሮ ግን የወያኔ ውሸቶች ተጋልጠዋል ። ወያኔ ጠላት ነውና ውሸቱ የሚጠበቅ ነው። ትግላችንን የጎዳው ግን ከህዝብ ጎራ ነን ብለው የሚዋሹትና የሚያደናግሩት ናቸው ።

ለአንዴም ቢሆን በዋልድባ አልዘፈን ብሏል ። እሳት ሲመጣ በሳር ውስጥ ገባሁ የሚለው በዝቷል ። ውሸት ካልንማ መዋሸት ከሚገደደው ወያኔ በላይ በሕዝብ ጎራ አለን የሚሉት ብሰዋል ። የትግልም ችግር ተውሳክ ሆነዋል ። ተቃዋሚ ነን እያሉ መሰረታዊ ትግላቸውን በሀሰት ላይ የመሰረቱ ጥቂት አይደሉም ። እውነቱ ተነግሮ ሳያልቅ ወደ ውሸቱ ዘልቀዋል። ውጤቱ መደናገር መሆኑ ደግሞ እየታየ ነው ። ተጎጂው ወያኔ ሳይሆን ሕዝብ ነው ። የሚፈታ ከተማ አዋጅ ቢነግሩበትም አይሰማ ዓይነት ሁኔታ አለ ። አሳሳቢ ነው ። ሕዝብን በውሸት ለማደራጀት መጣሩ በረጅሙ ውድቅ መንገድ ነው ። ሕዝብን በውሸት መሰረት ቀስቅሶ ማስነሣት የሚያዋጣ ቢመስልም፤ በሃቁ መንገድ መቀስቀስ ቢከብድም የሚያዋጣው መንገድ ሃቁ ነው ፡፡ ለዘላቂ ትግልም መሰረትና ዋስትና ነውና ። ሁሉም ያለውን ሁኔታ አውቆና ተገንዝቦ መርጦ ይታገላል ማለት ነው ። ሌላው አማራጭ ግን ሕዝብን ራሱን ማወናበድ ይሆናልና ፍሬያማ የሚሆን አይደለም ። ተቃዋሚ ነን ብለው ሕዝብን በሀሰት ሊያናውጡ የሚጥሩ ጥቂቶች አይደሉም ። ስንቶቹ ናቸው በስድስት ወር ውስጥ ወያኔን ልናወድም ነን ያሉን ? የ አርበኛነት ሰነድ መታወቂያ ሊሰጡን የተነሱት? በተልተሌ ጦር አመጣን ያሉት? ከ ኤርትራ ጦር አዘመትን ያሉት? ስንቴስ ተስፋ አደረግን? ስንቴስ ከሸፈብን? ተቃዋሚ ህይሎች ትግላቸውን ሃቅ ላይ መመስረት ሲገባቸው ሁለንተናቸው በውሸት በርኖስ የተጠቀለለ ሆኖ አለህ ሲሉት መና እየሆነ ተስፋ አስቀራጭ ሆኗል ቢባል ስህተት አይሆንም ። ውሸት በዝቷል ። ለሕዝብ መዋሸት ደግሞ ሕዝብን መናቅ ነው ። አያውቅብንም፤ እንጫውትበት ማለት ዓይነት ነው ። ውሎ አድሮ ግን ሕዝብ ያውቃል፤ ያታለሉትንም

ያወግዛል ። ታሪክ ይህንንም አሳይቷል ። ስለዚህም ትግልን በሀቅ ላይ መመስረት ተቀዳሚ መሆን አለበት። ከአገዛዙ ጋር በውሸት ውድድር ማድረግ ጎጂ ነው እንጂ ጠቃሚ አይደለም ። ውሸት ሕዝብን ይጎዳል እንጂ አያጠናክረውም ። ሕዝብን አታለንና አወናብደን ስልጣን እንይዛለን ባዮች ሁሉ ሲነጋ አታለልነው ያሉት ሕዝብ ይነሳባቸዋል ።

ኢሕአፓ በታህሳስ 1984 የሚከተለውን በመልዕክቱ ጽፎ ነበር---

“ ወያኔ ራሱ የምኒሊክ ሀውልት እንዲፈርስ ባለሟሉን ገፋፍቶ እያስለፈ/እያስጠየቀ አልነበርኩበትም ይላል ። ዓይን ያወጣ ውሸት! ቅጥፈት!

ሕዝብን እርሱ በርሱ በሚያናክስ ቅስቀሳ ላይ እየተሰማራ ሰላም ጠባቂ መስሎ ለመቅረብ ይጥራል ። ሌላ ውሸት!

ሰላም ሰፍኗል ይላል ።ዴሞክራሲን ገድቦ የዴሞክራሲ ብርሃን ደመቀ ይላል ።እየገነጣጠለ ለአንድነቱ ጠበቃ ነኝ ይለናል ። ራሱ ወስኖ ሌላ ወሰነ ይላል ። ቅጥፈት! ውሸት! የማያባራ ወያኔያዊ ተግባር!

በሀሰት ወሬ መከፋፈል፤ በሀይል ተጠቅሞ ማፈን መነጣጠል፤ በፕሮፓጋንዳ ማደናገር፤መለስተኛ ቅራኔዎችን አፋፍሞ ሕዝብን መገነጣጠል፤ድርጅቶችን መፍጠርና ያሉትን መሰነጣጠቅ፤ በ አሉባልታ መጠቀም፤በስም ማጥፋት ዘመቻ መሰማራት፤ በጥቅም በሹመት መደለል መከፋፈል ወዘተ ነው ስልታቸው” ።

ይህ የተጻፈው ከ አያሌ ዓመታት በፊት ቢሆን የዛሬም ሀቅ ነው ። ወያኔ አልተለወጠም--መሰረታዊና ቋሚ ማንነቱ የሚገለጠው በዓይን ዓውጣ ውሸቱ ነው። ይህን ቅጥፈቱን አመን እያሉ የሚወናበዱሉት አሉ። ሳያውቁ ቀርቶ ሳይሆን ሆዳቸው ሀሰቱን ሀቅ ብላችሁ ተኮልኮሉ ተሞኙ ስለሚላቸው ነው ። በመሆኑም ለጠነዛ የወያኔ ሀሰት ሆነ ሌሎችም ለሚነዙት ውሸት ሰለባ የሚሆነው ዜጋ ቁጥር ቀላል አይደለም ። አይኑን ከፍቶ እየተሞኘ ይበዘበዛል፤ ይታለባል ማለት ነው ። ለዚህም ነው ገና ያኔ በ 1984 ኢሕ አፓ ባሰራጨው መልክት ላይ ይህንን ያሰፈረው==

“ እና ዴሞክራሲ ስንል መሰረታዊ መብቶች አለምንም ገደብ የሚረጋጡበትን ስርዓት በመሆኑ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የአፍ እላፊ ከሚል ፍርሓት ተላቆ ያመነበትን ለመናገር መብቱ የተጠበቀ መሆን አለበት ። የንግገር ነጻነት ያልነውም የ ጽሁፍንም ነጻነት ይመለከታል ።. ዴሞክራሲ ስንል አንድ ሀይል ወይም ፓርቲ በስልጣን ቁጢጥ ብሎ እንዳሻው የሚፈነጭበትን ስርዓት ባለመሆኑና ሕዝብ የመረጠውን ሕዝብ የሚሽርበት ስርዓት በመሆኑ መንግስትና ሀይል ከሕዝብ ውክልና ውጪ ሊኖር ከቶ አይችልም ። የሕዝቡ ማህበራትና ሕዝባዊ ድርጅቶችም ከመንግስት ቁጥጥር ፍጹም ነጻ በሆነ መንገድ ተቋቁመውና በዚሁ ነጻ ይዘት ለመንቀሳቀስ እድል እስካለገኙ ድረስ መብት ተከብሯል ማለት አይቻልም ። የመብት ህልውና ህይወት የሚለካውም ምን ያህል ተቃዋሚ ሀይሎች፤ተጻራሪ ሀሳቦች ነጻነት አግኝተው ሊንቀሳቀሱና ሊሰሙ እንደቻሉ በመመዘን እንጂ የገዢው ሀይል ደጋፊዎች መቧረቅ መቻላቸውን በማየት ባለመሆኑ የተለየ ሀሳብና አቋም ያላቸውን ድርጅቶች ህጋዊ ህልውና መከልከል፤ ተቃውሞ ሊያሰሙ የፈለጉትን ማፈን፤ እንዳይሰባሰቡ እንዳይደራጁ ማገድ፤ የተለመደውን ምስጢራዊና የገሀድ የእመቃና አፈና እርምጃዎችን በተቃዋሚዎች ላይ መውሰድ ፤ገዢዎች ባዮች ዴሞክራሲያዊ ቢሉትም እኛ ግን ጭራሽ ጸረ ዴአክራሲያዊነት ነው የምንለው።”

ይህን የዴሞክራሲ ይዘት በሁሉም ገጽታው ወያኔ በባዕዳን ድጋፍ ለስልጣን ሲበቃ ጀምሮ የገለጥነውና ላልተሸራረፈ ዴሞክራሲ ትግላችንም የሚቀጥል መሆኑን ያስረገጥነው ነው ። ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ደብዛው ጠፍቶ ባለበት ቅጥረኞች ዛሬም ከወያኔ ጎን ተኮልኩለውና ምርጫ ብለው ሕዝብን ሊያደናግሩ እያሴሩ ናቸው። ግን አይሳካላቸውም ። ከወያኔ ጎን የሚቆሙትን

**ማንኛውም ተለጣፊ ሀይሎች ሕዝብ ህክ እንትፍ ይላቸዋል-- ለነገሩ ወያኔም ይጠቀምባቸዋል እንጂ መስክ አይሰጣቸውም ። ባለፈው አንድ ተቃዋሚ ነኝ ባይ ለይስሙላ ፓርላማ ወንበር በቅቷል==ነገ ሀያና መቶም ተመረጡ ቢባሉ ዋጋና ሚዛን የላቸውም። ጦሩ በማን እጅ ነው? ሁሉን ተቆጣጣሪ ማን ነው? ለመሆኑ ፓርላማ ተብዬው ነው ? ሀቁን ሕዝብ ያውቀዋል። መሞኘቱ የሚፈልጉ ተጠቃሚዎች ናቸው ። የይስሙላ ዴሞክራሲን ማጋለጥና ትግልን መቀጠል ደግሞ የሕዝብ ግዳጅ ነው።**

**ጸረ ወያኔው ትግላችን ይፋፋም !**